# የምሥራቁ ኮከብ

## ለልጆች የሚሆን ታሪክ

ከደረሰ ብሩ

ራዕይ አሣታሚ
አዲስ አበባ 1992 ዓ.ም.

# የምሥራቁ ኮከብ


በደረሰ ብሩ

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ. 101539
አዲስ አበባ

IM: RP – 05

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Are Reserved

«ተመልከት! ተመልከት!» አለ ሼታር የሜሬስን ትከሻ ይዞ እየነቀነቀ።



ሚሬስ፡-«ምንድን ነው እርሱ?» አለ። ቀጠለና በተከፈተው መስኮት ወደ ውጪ ተመለከተ።

ሌላው ጓደኛቸው ተርሺሽም የሼታርን ድምፅ ስለ ሰማ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ መስኮቱ ሄደ።



ሜሬስ፡- «ታያላችሁ ያንን ኮከብ? ታያላችሁ?» አለ በጣቱ ወደ ውጪ እያመለከተ።



«እስቲ ቆይ፥ አይታየኝም። መስኮቱን በደንብ ክፈተው።»

ተርሺሽ፡- «ያውና ይታየኛል። ከሌሎቹ ኮከቦች ሁሉ የተለየ ነው።»

«ልክ ናችሁ። ልክ ናችሁ። ለእኔም ይታየኛል። ያውና» አለ ሜሬስ ድምፁን ከፍ አደረገና።

ኮከቡ ከሌሎች ኮከቦች ሁሉ የተለየ ነው። በጣም ያምራል። ብልጭ! ብልጭ! ብልጭ! ይላል።

«ኑ ወደ ውጪ ወጥተን በደንብ እንየው» አለ ሼታር ለሁለቱ ጓደኞች።

ከዚያም ተርሺሽ፥ ሜሬስና ሼታር ተከታትለው ከቤት ወጡ።

ተርሺሽ፡- «ይገርማል! እንደዚህ ያለ ኮከብ ከዚህ በፊት አላየንም»





«አዎን፥ የተለየ ኮከብ ነው።
ደግሞ አሁን ከቅድም ይልቅ ያበራል። ወደ እኛም እየቀረበ የሚመጣ ይመስላል» አለ ሜሬስ።

«ኧረ ልክ ነህ ሜሬስ። ወደ እኛ አቅጣጫ እየመጣ ነው» አለ ሼታር።



«እስከ ዛሬ ድረስ ኮከቦችን ስንመለከት የዚህ ዓይነት ኮከብ አጋጥሞን አያውቅም መሰለኝ። እናንተ እንዳላችሁት በጣም እየቀረበ መጥቶአል» አለ ተርሺሽ። ልቡ በደስታና በመደነቅ ስሜት ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! አለ።

ሼታር፦ «የትኛው ኮከብ እንደሆነ ታውቃላችሁ? አዎን፥ ከብዙ ዓመታት በፊት የከዋክብት ተመራማሪ የነበረው ማሉሽታ ስለዚህ ኮከብ ነግሮኝ ነበር» እኔም በተራዬ ለሁለታችሁ ነግሬአችሁ ነበር። የአንድ ንጉሥ መወለድን የሚያሳየው ኮከብ እኮ ነው» አለ።

ሜሬስ፦ «ያኔ ከሩቅ እናየው የነበረው ኮከብ?»

ሼታር፦ «አዎን።»

ተርሺሽ፦ «አሁን ገና ገባኝ። አዎን፥ እርሱ መሆን አለበት።»

ሼታር፦ «ንጉሥ የሚሆነው ሕፃን በቅርቡ ሳይወለድ አልቀረም። ለማንኛውም የኮከቡን መጨረሻ ማየት አለብን።»

«ምን ማለታችሁ ነው? እየተጠጋ መጣኮ» አለ ሜሬስ ጮክ ብሎ።

ተርሺሽ፦ «ይህንን አስገራሚ ሕፃን ሄደን ማየት አለብን። በቶሎ ሄደን ማየት አለብን።»

ሜሬስ፦ «እኔም ደስ ይለኛል። በፍጥነት ብንሄድ ጥሩ ነው።»

ሼታር፦ «እኔ በሐሳቡ እስማማለሁ። ሜሬስ አንተስ?»



ሼታር፡- «ታዲያ ለሕፃኑ የምንሰጠውን ስጦታ ብናዘጋጅ ምን ይመስላችኋል?»

ተርሺሽ፡- «ምን እናዘጋጅ?» ሜሬስ፡- «ወርቅ ቢሆንስ?»

ሼታር፡- «ወርቅ ጥሩ ነው። ዕጣንና ከርቤም ብንጨምር ጥሩ አይመስላችሁም?»

«ጥሩ ነው» አለ ተርሺሽ። ሜሬስም በሐሳቡ ተስማማ።

ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ኮከቦችን የሚመረምሩ ዐዋቂዎች ናቸው። በኮከቦች አማካይነት አንዳንድ ሁኔታዎችን ይረዳሉ። በተለይ የምሥራቁን ኮከብ ስላዩ ደስ አላቸው።



የተወለደውን አስደናቂ ሕፃን ለማየት ተዘጋጁ። ወርቅ፥ ዕጣንና ከርቤ አዘጋጁ። ቆንጆ በሆኑ ትንንሽ ሣጥኖች አስቀመጡአቸው። ለመንገድ የሚሆን ምግብ አዘጋጁ። ግመሎቻቸውን ጫኑ።



ኮከቡ ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ወዳሉበት አካባቢ በጣም ተጠጋ። ብልጭ! ብልጭ! ብልጭ! አለ። ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ደስ አላቸው። ለተወለደው ሕፃን ያዘጋጁትን ስጦታና በመንገድ የሚበሉትን ምግብ ይዘው በግመሎቻቸው ላይ ተቀመጡ።

የሼታር፥ የሜሬስና የተርሺሽ ግመሎች ተንቀሳቀሱ። ኮከቡም አብሮ ተንቀሳቀሰ። ከሌላ ጊዜ የበለጠ ብሩህ ሆኖ ታያቸው። ኮከቡ የሚጓዘው ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ነበር።



ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ኮከቡ ስለሚመራቸው ተገረሙ። በጣምም ደስ አላቸው። ተቀምጠው ምግብ ሲበሉ ኮከቡ ቆሞ ይጠብቃቸው ነበር። ደክሞአቸው ዕረፍት ሲያደርጉ ኮከቡ ቆሞ ይጠብቃቸው ነበር። መሄድ ሲጀምሩ ኮከቡ ፊት ፊት እየቀደመ ይመራቸው ነበር።



ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ በግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው ተጓዙ። ወንዞችን ተሻገሩ። ተራራዎችንና ኮረብታዎችን አቋረጡ። ጥሩ ጥሩ ዛፎችንና አበቦችን አዩ። ደስ የሚሉ ወፎች መዝሙር ሲዘምሩ ሰሙ። ወፎቹ አረንጓዴ፥ ብጫ፥ ቀይ፥ ሰማያዊና ቡና ዓይነት መልክ ነበራቸው። ሦስቱ ሰዎች በጫካ ውስጥ ሲሄዱ አንበሶች፥ ተኩላዎች፥ ነብሮች፥ ድኩላዎች፥ ጥንቸሎች፥ ጦጣዎች አዩ። ሕፃኑን ንጉሥ ስለሚያዩ እጅግ በጣም ደስ አላቸው።

ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ከጥቂት ቀን በኋላ አንዲት ከተማ ደረሱ። ከተማይቱ በይሁዳ አገር የምትገኝ ኢየሩሳሌም የምትባል ነበረች። ሰዎቹ እንግዶች እንደሆኑ ሁሉም ሰው ዐወቀ። ሁሉም ዘወር እያለ ተመለከታቸው። መልካቸው የተለየ ነው። አለባበሳቸው የተለየ ነው። እነርሱም፡– «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ልንሰግድለት መጥተናል» እያሉ አንዳንድ ሰዎችን ይጠይቁ ነበር። ከተጠየቁት መካከል አንዱ ሰውዬ ንጉሥ ከተወለደ ወደ ቤተ መንግሥት ሂዱ ብሎ መከራቸው።





በዚያን ጊዜ ሄሮድስ የተባለ ንጉሥ በኢየሩሳሌም ከተማ ነበረ። ንጉሥ ሄሮድስ የሼታር፥ የሜሬስና የተርሺሽ በኢየሩሳሌም ከተማ መኖር ሰማ። ስለ ንጉሡ መወለድ ሰማና ደነገጠ። የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎችን አስጠርቶ፦ «ክርስቶስ የሚወለደው ወዴት ነው? ከመጻሕፍት ያነበባችሁትን ንገሩኝ» አላቸው። የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎችም «ክርስቶስ በቤተልሔም ይወለዳል ተብሎ ተጽፎአል» አሉት።

ቀጥሎ ሄሮድስ፥ ከምሥራቅ አገር የመጡት ሦስቱን ሰዎች በስውር አስጠራቸው። ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ወደ ንጉሥ ሄሮድስ ቤተ መንግሥት ሄዱ። «እናንተ፥ በዚህ አገር ንጉሥ እንደ ተወለደ ታውቃላችሁ ይባላል። እውነት ነው?» አላቸው።



«አዎን፥ ንጉሥ ሆይ፥ በዚህ አገር ንጉሥ እንደተወለደ ኮከቡ አስረድቶናል» አሉ ሦስቱም በአንድነት። «ኮከቡን ያያችሁት መቼ ነው?» አለ ንጉሥ ሄሮድስ። ሦስቱ ሰዎች «ንጉሥ ሆይ ኮከቡን ያየነው በቅርብ ጊዜ ነው» አሉ። ንጉሥ ሄሮድስ፦ «በቶሎ ሂዱና ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ፈልጉ። ባገኛችሁት ጊዜ መጥታችሁ ንገሩኝ። እኔም ሄጄ እሰግድለታለሁ» አለ።



ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ፦ «እሺ ንጉሥ ሆይ፥ ያዘዝኸንን እናደርጋለን» አሉና ንጉሡን ተሰናብተው ከቤተ መንግሥት ወጡ።



ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ከቤተ መንግሥት እንደወጡ ንጉሥ ሄሮድስ ከትልቁ መቀመጫው ዘሎ ተነሣ። በጣም ተቆጣ። ፊቱ ተለወጠ። «ወይኔ ሄሮድስ! እንዴት ሌላ ንጉሥ ተወለደ ይላሉ? እኔ እያለሁ ሌላ ንጉሥ አይነግሥም! በጭራሽ አይነግሥም! አይሆንም!» አለ።

እርሱን ለመጠበቅ በአጠገቡ የቆመው ወታደር የያዘውን ሰይፍ ለቀም አደረገ። ገልበጥ ገልበጥ አደረገው። ሰይፉ ብልጭልጭ ብልጭልጭ አለ።

ሄሮድስ ሰይፉን እንደያዘ ወደ ትልቁ መቀመጫው ሄደና ተቀመጠ።

«ቆይ ብቻ! እነዚያ ከምሥራቅ አገር የመጡ ሰዎች ወደዚህ ተመልሰው ሕፃኑ ያለበትን ቦታ ይንገሩኝ። ከዚያ በኋላ የማደርገውን እኔ ዐውቃለሁ» አለ።

ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ በኮከቡ እየተመሩ ቤተልሔም ወደ ተባለችው ትንሽ ከተማ ሄዱ። የምሥራቁ ኮከብ ቦግ! ቦግ! ቦግ! እያለ በአንድ ቤት ላይ መጥቶ ቆመ።



«ያውላችሁ! ኮከቡ እኮ ቆመ። ሕፃኑ የተወለደው እዚያ ቤት መሆን አለበት» አለ ተርሺሽ።

«እውነትህን ነው ተርሺሽ፥ ተነሡ፥ ወደዚያው እንሂድ» አለ ሼታር።



ሦስቱ የምሥራቅ ዐዋቂዎች ከግመሎቻቸው ወረዱ። የግቢውን በር አንኳኩተው ገቡ። የተወለደውን ሕፃንና እናቱን አገኙ። በመሬት ላይ ወድቀው ሰገዱለት። ሣጥኖቻቸውን ከፍተው ወርቅ፥ ዕጣንና ከርቤ አቀረቡለት።





ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ለሕፃኑ ስጦታ ካቀረቡ በኋላ እንዲህ ብለው ዘመሩለት፦

እኛ የምሥራቅ ጠቢባን፥
ገና ሳለን በአገራችን፥
ብሩህ ኮከብህን ዐይተን፥
ወርቅ፥ ዕጣንና ከርቤ ይዘን፥
ልንሰግድልህ መጣን።
ስለ በቃን ለዚህ ዕድል፥
እጅግ ደስ ብሎናል።
የአይሁድ ንጉሥ የዓለም ብርሃን፥
የመጣህ ልታድን ሰውን፥
ኢየሱስ ክብር ለአንተ ይሁን።

ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ሕፃኑን ተሰናብተው ወጡ። ደስ እያላቸው ከቤቱ ወጡ። ሌሊቱን ወደሚያድሩበት ሄዱ። ሌሊት በሕልም እግዚአብሔር ተናገራቸው። «ሄሮድስ ሕፃኑን ለመግደል ይፈልጋልና ወደ እርሱ አትመለሱ» አላቸው።

ሼታር፥ ሜሬስና ተርሺሽ ጠዋት ከእንቅልፋቸው ነቅተው ስለ ሕልሙ ተነጋገሩ። በሌላ መንገድ ወደ

አገራቸው ለመመለስ ተማከሩ። በግመሎቻቸው ተቀምጠው ጉዞ ጀመሩ። ከቤተልሔም ወጥተው ሄዱ።

የምሥራቁ ኮከብም ሕፃኑ ከነበረበት ቤት ወደ ላይ ወጣ። ወደ ላይ እየራቀ ሄደ። ለዓይን እየተሰወረ ሄደ። ብልጭ! ብልጭ! ብልጭ! እያለ ሄደ የምሥራቁ ኮከብ።